# 2018 2019 የትምህርት ቤት ምደባ ዝውውር

## Change of School Assignment (COSA)

### የመረጃ መጽሔት

## መግቢያ

በሞንጎመሪ ካውንቲ ተማሪዎች በመኖሪያ አካባቢያቸው በሚገኝ የአካባቢ ት/ቤት ወይም በግላዊ የትምህርት ፕሮግራም (IEP) ምክንያት በተመደቡበት ት/ቤት እንዲከታተሉ ይጠበቅባቸዋል። ተማሪዎች ከአካባቢ ት/ቤት ወይም በግላዊ የትምህርት ፕሮግራም IEP ሂደት ምክንያት ከተመደቡበት፣ በሚከተሉት መመዘኛዎች/መስፈርት መሠረት ወደ ሌላ ት/ቤት ለመቀየር (COSA) ማመልከት ይችላሉ፡-

- የተለየ አስቸጋሪ ሁኔታ- በማስረጃ የተደገፈ ልዩ ችግር/አስቸጋሪ ሁኔታ ሲቀርብ በአብዛኛው ቤተሰብ ውስጥ የሚከሰቱ የተለመዱ ዓይነት ችግሮች እንደልዩ ችግር አይቆጠሩም።
- የቤተሰብ ዝውውር-ቤተሰብ በሞንጎመሪ ካውንቲ ውስጥ ቦታ ሲቀይሩ ባሉበት ት/ቤት ለመቆየት ከመረጡ የትም ህርት ዓመት እስከሚያልቅ ድረስ ብቻ ለመቆየት ይቻላል፣ ለ11ኛ ክፍል ተማሪዎች ብቻ በልዩ አስተያየት እስከ ሚመረቁ ድረስ ባሉበት ለመቀጠል ይፈቀድላቸዋል።
- ወንድም/እህት-በመደበኛ/አጠቃላይ የትምህርት ፕሮግራም ወይም ልዩ የትምህርት ፕሮግራም ትልቅየው/ዋ ወደሚ ገባበት/ወደምትገባበት ት/ቤት ታናሽየው/ዋ ም ለመከታተል ከፈለገ/ች፣ በዓመቱ ውስጥ ትንሹ/ሹ ሊገባ/ልትገባ ይችላል/ትችላለች።
  - » ታላቅ ወንድም/እህት ማግኔት፣ የቋንቋ ኢመርሽን፣ ወይም ሌላ የመተግበርያ ፕሮግራም ሲ(ስት)ከታተል፣ አንድ-በ-አንድ እታየ ለታናሽ ወንድሞች/እህቶች ለመደበኛ የት/ቤት ፕሮግራም COSA ሊፈቀድ ይችላል። የዚህ አይነት ፈቃድ በመማርያ ክፍል ቦታ የመኖር፣ የክፍል-ደረጃ ምዝገባ፣ የሰራተኛ አመዳደብ፣ ወይም በሚመለከታቸው ት/ቤቶች ላይ ተፅእኖ የሚያሳድሩ ሌሎች ታሳቢዎች ግንዛቤ ዉስጥ መግባት አለባቸው።

---

እነዚህ ተማሪዎች ለመዛወር የሚጠይቁት ት/ቤት በራሳቸው ክልል ዙርያ/ኮንሰርሺየም/CONSORTIUM ከሆነ COSA ማቅረብ አይኖርባቸውም።

- በሰሜን ምስራቅ ክልል ዙርያ/Northeast Consortium (NEC) የሚኖሩ ተማሪዎች ወይም ከታችኛው ካውንቲ ክልል ዙርያ Downcounty Consortium (DCC) ወደ ሌላ ክልል/Consortium የሚጠይቁ ከሆነ።
- በመካከለኛ ደረጃ ማግኔት ክልል/Middle School Magnet Consortium (MSMC) ነዋሪ የሆኑ የመካከለኛ ደረጃ ት/ቤት ተማሪዎች በMSMC የምልመላ ሎተሪ ሂደት ያለፉና ወደ ሌላ መካከለኛ ደረጃ ት/ቤት ማግኔት ክልል (MSMC) ለመግባት የሚያመለክቱ፡ ፡

በክልሉ ውስጥ ሌላ ት/ቤት ከጠየቁ (within the Consortium)፣ ለክልል/ለኮንሰርሺያ ምርጫ እና ማመልከቻ ፕሮግራሞች ክፍል (DCCAPS), 11721 Kemp Mill Road, Silver Spring, Maryland 20902፣ የተፈረመበት የጽሑፍ ማመልከቻ ማቅረብ ያስፈልጋል። በ NEC፣ DCC፣ ወይም MSMC ውስጥ ት/ቤቶችን የመቀየር ኢንፎርሜሽን ለማግኘት፣ DCCAPS በስልክ ቁጥር፡- 240-740-2540 ያግኙ፣ ወይም የሚከተለውን ድረ-ገጽ ይጎብኙ www.montgomeryschoolsmd.org/departments/schoolchoice{14}።

---

እባክዎ ያስታውሱ፡- COSA ን ከተቀበሉ ወላጅ ወይም ሞግዚት መጓጓዣ/ትራንስፖርት መስጠት አለባቸው።


የተማሪዎች ሠራተኞችና ክትትል አገልግሎቶች ክፍል (DPPAS)

301-315-7335 Fax (ፋክስ)፡- 301-279-3971

# በተደጋጋሚ የሚነሱ ጥያቄዎች

- **ት/ቤት ለመቀየር እንዴት ማመልከት እችላለሁ?**

  የMCPS ቅጽ 335-45፣ Request for Change of School Assignment/የት/ቤት ምደባ ለውጥ ጥያቄ (COSA){19}፣ በዚህ መጽሔት ውስጥ ተካትቷል። ቅጹ በሚከተለው ድረ-ገጽም ላይ ይገኛል www.montgomeryschoolsmd.org/info/transfers/ እና በስድስት ተጨማሪ ቋንቋዎች ይገኛል። ቅጹን ሞልተው የመኖርያ ማረጋገጫና ለፊርማ በርእሰ መምህር እንዲታይ ወደ አካባቢዎ ት/ቤት ያቅርቡ። ት/ቤቱ ቅጹን/ማመልከቻውን ለማካሄድ(ለማስፈጸም) ወደ DPPAS ይልካል።

  ለት/ቤት ስርአት አዲስ የሆኑ ተማሪዎች የCOSA ጥያቄ ከማቅረባቸው በፊት በአካባቢያቸው ት/ቤት መመዝገብ አለባቸው። የCOSA ጥያቄዎች ተማሪው/ዋ የመኖርያ ማረጋገጫ እና የምዝገባ ሂደት በአካባቢ ት/ቤት እስኪ(ክት)ፈፀም ድረስ አይታዩም/አይገመገሙም።

- **ማመልከት ያለብኝ መቼ ነው?**

  ለ 2018–2019 የትምህርት ዓመት የ COSA ማመልከቻዎችን ለማቅረብ የሚቻለው ዝውውር ለማድረግ ከሚፈለገው አንድ የትምህርት ዓመት ቀደም ብሎ ባለው ፌብሯሪ 1 እና ኤፕሪል 1 መካከል ነው። ድረስ ለወላጆች/ሞግዚቶች እና ለተማሪዎች እስከ ሜይ 31ድረስ ውሳኔውን ለማሳወቅ የተቻለንን ሁሉ እናደርጋለን። ከኤፕሪል 1 በኋላ የሚቀርቡ የCOSA ማመልከቻዎችን ለመቀበል የሚቻለው ተማሪው/ዋ ለሞንጎመሪ ካውንቲ አዲስ ከሆነ/ች ብቻ እና ከኤፕሪል 1 በፊት የአስቸኳይ ጊዜ ሁኔታ ካለ ብቻ ነው። ይህን ሁኔታ የሚደግፍ ማስረጃ መቅረብ አለበት። COSA አመልክተው በሂደት ላይ ያሉ/የሚጠባበቁ ተማሪዎች የመጨረሻ ውሳኔ እስከሚሰጥ ድረስ በተመደቡበት ት/ቤት መከታተል አለባቸው።

- **የCOSA ጥያቄዬን ካቀረብኩ በኋላ ምን ሊሆን ይችላል?**

  በአካባቢ ት/ቤት ርእሰ መምህር ከተፈረመበትና የመኖሪያ አካባቢ ከተረጋገጠ በኋላ የ COSA ጥያቄ ወደ DPPAS (በዓመት ከ3,000 እስከ 4,000 ማመልከቻዎችን ይቀበላል) ይተላለፋል። ውሳኔ ከመሰጠቱ አስቀድሞ DPPAS መጣራት ያለባቸውን ነገሮች ያጠናቅቃል።

- **ጥያቄዬ መጽደቁን ወይም ውድቅ መደረጉን መቼ ነው የምሰማው?**

  ለወላጆች/ሞግዚቶች እና ለተማሪዎች ሜይ ላይ በደብዳቤ ለማሳወቅ የ DPPAS ሠራተኞች የተቻላቸውን ትረት ያደርጋሉ።

- **ልዩ ችግር ማለት ምንድን ነው?**

  የተለየ አስቸጋሪ ሁኔታ እንደየቤተሰቡ ግላዊ እና ሰብአዊ ሁኔታ ይለያያል። በአብዛኛዎቹ ቤተሰቦች ላይ የሚከሰቱ የተለመዱ ጉዳዮች፣ እንደ ሙዋዕለ ህፃናት ወይም ፕሮግራም/የኮርስ ምርጫዎች፣ አስገዳጅ ሁኔታ ካልተፈጠረ በስተቀር ከባድ ችግር ተደርጎ አይወሰድም። አስቸጋሪ ሁኔታን አስመልክቶ የሚቀርቡ ጥያቄዎች በሙሉ መቅረብ ያለባቸው ከማረጋገጫ ማስረጃ ጋር ነው፣ ያለበለዚያ ጥያቄው ተቀባይነት አይኖረውም።

- **ለ COSA ሳመለክት በአባሪነት ማቅረብ ያለብኝ ማስረጃዎች ምንድናቸው?**

  በግላዊ ሁኔታ ይለያያል፣ ለማንኛውም፣ የሚቀርቡት ማስረጃዎች ያመለከቱበትን ሁኔታ የሚያረጋግጡ መሆን አለባቸው። ለምሳሌ፦ የፋይናንስ ሠነዶች፣ ከጤና ባለሙያዎች የተጻፉ ደብዳቤዎች እና ከአሠሪዎች/ቀጣሪዎች የተጻፉ ደብዳቤዎች።

- **የዝውውር ሂደቱ ለጥንድ የአንደኛ ደረጃ/ኤሌሜንተሪ ት/ቤቶችም ተመሳሳይ ነው ወይ?**

  አዎን። ተማሪው/ዋ በ COSA የጸደቀ ጥንድ የአንደኛ ደረጃ/ኤለመንተሪ ት/ቤት በመከታተል ላይ የሚገኝ/የምትገኝ ከሆነ ለከፍተኛው ደረጃ የኤሌመንተሪ ት/ቤት ወዲያውኑ ለማፅደቅ እንዲቻል በፊት COSA ያጸደቀበትን ቅጽ ማቅረብ ያስፈልጋል።

- **ወደ ፑልስቪል ኤለመንተሪ ት/ቤት (Poolesville Elementary School) የተመደቡ እና ሞኖከሲ ኤለመንተሪ ት/ቤት (Monocacy Elementary School) ለመከታተል የሚፈልጉ ተማሪዎች አካሄዱ እንዴት ነው?**

  ወደያውኑ እንዲጸድቅ የ COSA ቅጽ ማቅረብ አለባቸው።

- **ልጄ ልዩ የትምህርት አገልግሎቶች በመቀበል ላይ የሚገኝ/የምትገኝ ከሆነስ?**

  በሁሉም ት/ቤቶች የሚገኙ ልዩ የትምህርት አገልግሎቶች የሚቀበሉ ተማሪዎች መደበኛ የCOSA ሂደት ይከታተላሉ። ሆኖም ግን፣ የተጠየቀው COSA ከፀደቀ፣ የመጓጓዣ/ትራንስፖርት አገልግሎት አይሰጥም። ሌሎች ልዩ የትምህርት ፕሮግራሞችን የሚከታተሉ ተማሪዎች በሙሉ የ COSA ቅጽ መጠቀም የለባቸውም። ጥያቄያቸውን ለልዩ ትምህርት አገልግሎቶች ጽ/ቤት በሚከተለው አድራሻ ማቅረብ አለባቸው።

  Department of Special Education Services at 850 Hungerford Drive, Room 230, Rockville, Maryland 20850 በሁሉም ት/ቤቶች የማይገኙ ልዩ የትምህርት አገልግሎቶች በመቀበል ላይ ለሚገኙ ተማሪዎች የሚደረጉ ጥያቄዎች የሚመለከቱ ውሳኔዎች ከ ጁላይ 1 በኋላ ይደረጋሉ። ለተጨማሪ መረጃ፣ እባክዎን 301-279-3837 ይደውሉ።

- **COSAዎች ለአክዴሚዎች፣ የፊርማ/signature ፕሮግራሞች፣ ወይም ለልዩ ኮርሶች ይፈቀዳሉ ወይ?**

  የለም። የፊርማ/signature ፕሮግራሞች እና ልዩ ኮርሶች ለሚገኙበት ት/ቤት ነው የተተለሙት። ወደነዚህ ት/ቤቶች የሚደረጉ የCOSA ጥያቄዎች ከሁሉም ሌሎች የCOSA ጥያቄዎች ጋር ተመሳሳይ መስፈርቶች ማሟላት አለባቸው። ሂደቱ የማይመለከታቸውን ፕሮግራሞች ምሳሌዎችን በዚህ መጽሔት ገጽ 2 ላይ ይመልከቱ።

- **ወደ አዲሱ ት/ቤት ትራንስፖርት ይቀርባል ወይ?**

  አይደለም። የመጓጓዣ/ትራንስፖርት አገልግሎት መስጠት የወላጅ/የሞግዚት ኃላፊነት ነው።

- **በአዲሱ ት/ቤት ልጄ በት/ቤቶች የስፖርት ውድድር ለመጫወት ብቃት ይኖረዋል/ራታል ወይ?**

  ከመጋቢ ትምህርት ቤታቸው ውጪ COSA ያገኙ የሁለተኛ ደረጃ ት/ቤት ተማሪዎች በአትሌቲክስ ለመሳተፍ (አትሌቲክስ እንዲሠረዝላቸው ካላመለከቱ በስተቀር) በአዲሱ ት/ቤት ለአንድ ዓመት መማር አለባቸው። ወደ አዲስ መጋቢ ሁለተኛ ደረጃ ት/ቤት COSA የተሰጣቸው የመካከለኛ ደረጃ ተማሪዎች በሽግግሩ ወቅት በአዲሱ ት/ቤት ለመቀጠል ከፈለጉ እንደገና ማመልከት ይጠበቅባቸዋል። ነገር ግን አትሌቲክስ ለመሳተፍ ያለመቻላቸው ገደብ ወዲያውኑ ይሰረዝላቸዋል። የበለጠ መረጃ ለማግኘት የአትሌቲክስ ዲፓርትመንትን በስልክ ቁጥር 240-453-2594 ይጠይቁ።

- **ልጄ ለCOSA አንዴ ከተፈቀደለ(ላ)ት፣ በየአመቱ ማመልከት ያስፈልገኛል ወይ?**
  - COSA ያጸደቀው ለአንድ ዓመት ብቻ ካልሆነ በስተቀር ተማሪው/ዋ በሚቀጥለው የትምህርት ደረጃ በተማሪነት እስኪመዘገብ/እስክትመዘገብ ድረስ በ COSA ለመቆየት ይችላል/ትችላለች።
  - አዲስ የCOSA ቅጽ ማቅረብ አስፈላጊ ቢሆንም፣ በCOSA የጸደቀ የመካከለኛ ደረጃ/ሚድል ስኩል ተማሪ ወደ መጋቢ ሁለተኛ ደረጃ ት/ቤት በቀጥታ ለመግባት ይችላል/ትችላለች።
  - በ COSA ያሉ የኤለመንተሪ ተማሪዎች ሌላ የ COSA ማመልከቻ ማቅረብና በአካባቢ ት/ቤት ለመከታተል ስለማይ(ት)ችል የተለየ መካከለኛ ደረጃ ት/ቤት (ሚድል ስኩል) መግባት አስፈላጊ/ግድ የሆነበ(ባ)ትን ምክንያት ማረጋገጫ መስጠት አለበት/አለባት።
- **ልጄ ለCOSA አንዴ ከተፈቀደለ(ላ)ት፣ ውድቅ ሊደረግ ይችላል ወይ?**

  አንድ ርእሰመምህር፣ ለምሳሌ ቀጣይ የዲሲፕሊን ግድፈቶች ወይም የመከታተል/የመቅረት ጉዳዮች ካሉ፣ አድን COSA ውድቅ እንዲሆን ሊ(ልት)ጠይቅ ይችላል/ትችላለች።
- **ሌሎች ማናቸውም ፕሮግራሞች ከ COSA አፈጻጸም የተለዩ ናቸው?**

  የሚከተሉት ለምሳሌ ከ COSA የምልመላ ሂደት የተለዩ ናቸው ቢሆንም ግን፣ ሌላ የምልመላ መስፈርት ሊኖራቸው ይችላል።
  - በሞንጎመሪ ብሌር ሁለተኛ ደረጃ ት/ቤት የሚገኙ የሳይንስ፣ ሂሳብ፣ እና የኮምፒውተር ሳይንስ ማግኔት ፕሮግራም/ Magnet program at Montgomery Blair High School።
  - በአልበርት ኢይንስታይን ሁለተኛ ደረጃ ት/ቤት ሥዕላዊ የስነጥበብ ማዕከል/The Visual Art Center at Albert Einstein High School
  - በሪቻርድ ሞንጎመሪ ሁለተኛ ደረጃ ት/ቤት ዓለም አቀፍ ባካሎሬት ማግኔት ፕሮግራም/The International Baccalaureate Magnet program at Richard Montgomery High School
  - በፑልስቪል ሁለተኛ ደረጃ ት/ቤት የማግኔት ፕሮግራሞች/ Magnet programs at Poolesville High School
  - በሮቤርቶ ክለሚንቴ የላይኛው ካውንቲ ማዕከል ፕሮግራሞች/ Upcounty Center programs at Roberto W. Clemente Middle School
  - በኢስተርን መካከለኛ ደረጃ ት/ቤት የሰብአዊ ጥናቶች እና ኮሙኒኬሽን ማግኔት ፕሮግራም/The Humanities and Communication Magnet program at Eastern Middle School
  - የታኮማ ፓርክ መካከለኛ ት/ቤት የሳይንስ፣ ሂሳብ፣ እና የኮምፒውተር ሳይንስ ማግኔት ፕሮግራም/The Science, Mathematics, and Computer Science Magnet program at Takoma Park Middle School
  - የዳበሩ ትምህርቶች ማእከሎች
  - በጥዋቱ የመለየት ፕሮግራም ለተቀዳሚ ባለ ክፍተኛ ተሰጥኦ በTakoma Park Elementary School
  - በማንኛውም የኤሌሜንታሪ ወይም መካከለኛ ደረጃ ት/ቤት የቋንቋ ኢመርሽን ፕሮግራም የተመደቡ ተማሪዎች
  - ሌሎች ፕሮግራሞች፣ በት/ቤቶች ዋና ተቆጣጣሪ እንደተገለጸው
  - ሌሎች ፕሮግራሞች አማራጮች/OPTIONS ላይ እንደተገለጸው፡- የካውንቲ አቀፍ ፕሮግራሞች መመሪያ (www.montgomeryschoolsmd.org/departments/enrichedinnovative/options)

  ልዩ/የታለፈላቸዉ/የተተወላቸዉ ፕሮግራም በመከታተላቸው ምክንያት COSA የፀደቀላቸው ፕሮግራሙን ካቋረጡ/ከተውት ወደ አካባቢ ት/ቤቶቻቸው መመለስ ይጠበቅባቸዋል። (ይመልከቱ፡- www.montgomeryschoolsmd.org/departments/enrichedinnovative/.)
- **የኔ COSA ውድቅ ተደረገ። እንዴት አድርጌ ነው ይግባኝ የምለው?**

  ለOffice of the Chief Operating Officer, 850 Hungerford Drive, Room 43, Rockville, Maryland 20850 በጽሑፍ ይግባኝ መጠየቅ ይቻላል። ዋናው ስራ አስኪያጅ/chief operating officer እንደ ት/ቤት የበላይ ተቆጣጣሪ ተወካይ ሆኖ ያገለግላል። ይግባኙ በጽሑፍ ለዋና የሥራ ኃላፊ ጽ/ቤት በውሳኔ ደብዳቤ ላይ በተጠቀሰው ቀን መነሻ አሥራ አምስት ቀን ውስጥ መድረስ አለበት። ይግባኝ እንዲታይ ያስፈለገበትን ምክንያት መገለጽ አለበት። ይግባኝ ለመጠየቅ ተጨማሪ ኢንፎርሜሽን መስጠት ላይኖርብዎት ይችላል። ነገር ግን ቢታይ ይጠቅመኛል የሚሉትን ተጨማሪ መረጃ እንዲታይልዎት ለማቅረብ ይችላሉ። ለተጨማሪ መረጃ በስልክ ቁጥር፡- 240-314-4880 ይደውሉ። የCOSA ይግባኝ ላይ ውሳኔ የሚጠባበቁ ተማሪዎች የመጨረሻ ውሳኔ እስኪሰጥ ድረስ በተመደቡበት ት/ቤት ይከታተላሉ።

  ሁሉም ይግባኞች የሚታዩት በቀረቡት ሠነዶች እና በቴሌፎን ኮንፈረንሶች ነዉ።

  በዋናው የሥራ ኃላፊ የእርስዎ ይግባኝ ውድቅ ከተደረገ፣ በጽሑፍ ወደሞንጎመሪ ካውንቲ የትምህርት ቦርድ Montgomery County Board of Education (Board), 850 Hungerford Drive, Room 123, Rockville, Maryland 20850 ምንም እንኳ በተቻለ ፍጥነት ይግባኝዎን ማቅረብ እንዳለብዎት ብናደፋፍርም፣ ዋና የሥራ ኃላፊው ውሳኔ በደብዳቤ ከተገለጸበት በ30 ቀናት ውስጥ ማቅረብ ያስፈልጋል። ሁሉም ይግባኞች የሚሰሙት በቦርዱ መደበኛ የስብሰባ ቀናት ነው። ቦርዱ አገስት ላይ ስብሰባ እንደማያደርግ እባክዎ ይገንዘቡ።

ማስታወሻ፡- ከጁላይ 1/ 2018 አስቀድሞ ወደ ዋናው የሥራ ኃላፊ ጽ/ቤት የደረሱ ይግባኞች የትምህርት ዓመት ከመጀመሩ በፊት የመጨረሻ ውሳኔ ይሰጥባቸዋል። ከጁላይ1/2018 በኋላ ለደረሱ ይግባኞች የመጨረሻ ውሳኔ የትምህርት ዓመቱ ከተመጀመረ በኋላ ሊሰጡ ይችላሉ።

# ከምድብ ትምህርት ቤት ዝውውር መጠየቂያ
# Change of School Assignment (COSA)

የሞንጎመሪ ካውንቲ የህዝብ ት/ቤቶች (MCPS)
Rockville፣ Maryland 20850

MCPS ቅጽ 335-45
ዲሴምበር 2017

**መመሪያዎች፡-** ወላጅ/ሞግዚት ክፍል I ን ሞልተው ቅጹን ለተማሪው የአካባቢ ት/ቤት ርእሰ መምህር ከኤፕሪል 1, 2018 በፊት ማቅረብ አለባቸው። ቅጹን ከመሙላትዎ በፊት በምድብ ትምህርት ቤት ዝውውር (Change of School Assignment (COSA)) የመረጃ መጽሔት ላይ የሚገኘውን መረጃ በጥንቃቄ ያንብቡ። የትምህርት ቦርድ ፖሊሲ ይመልከቱ/Board of Education Policy JEE የተማሪ ዝውውሮች እና የሞንጎመሪ ካውንቲ የህዝብ ት/ቤቶች ደምብ/MCPS Regulation JEE-RA የተማሪ ዝውውሮች

**ክፍል I:- የምድብ ትምህርት ቤት ዝውውር ጥያቄ ማመልከቻ። በወላጅ/አሳዳጊ የሚሞላ። (እባክዎን ባለቀለም ብእር/በታይፐ ይጻፉ)**

ተማሪ ______________________________ የትውልድ ቀን ____/____/____
የመጨረሻ የመጠርያ/መጀመሪያ የመ.ፊ

የልዩ ትምህርት አገልግሎቶች በማግኘት ላይ (ነውን/ናትን?) አዎ ☐ አይደለም ☐

አሁን የሚማርበት/የምትማርበት ት/ቤት ______________________________ በሴፕቴምበር 2018 የገባበት/የገባችበት ክፍል ______

የአካባቢ ትምህርት ቤት ______________ የተጠየቀው ትምህርት ቤት ______________ ተፈጻሚ የሚሆንበት እለት ____/____/____

ወላጅ/አሳዳጊ፡- ______________________________

አድራሻ፡- ______________________________ የቤት ስልክ፡- ____-____-____
መንገድ

______________________________ የስራ ስልክ፡- ____-____-____
ከተማ ስቴት ዚፕ ኮድ

የኢ-ሜይል አድራሻ፡- ______________________________ የእጅ ስልክ፡- ____-____-____

በቤት ውስጥ የሚነገር ቋንቋ ______________________________ አስፈላጊ ነው TTY ☐

ጥያቄ የቀረበበት ምክንያት፡-

☐ የተለየ አስቸጋሪ ሁኔታ- እባክዎ በዝርዝር ይግለጹ። ማረጋገጫ ሠነድ ከዚህ ቅጽ ጋር አባሪ መደረግ አለበት።
☐ የቤረሰብ ዝውውር-ይህንን የትምህርት ዓመት ለማጠናቀቅ የሚቻለው በቤተሰብ ዝውውር ምክንያት ብቻ ነው።
☐ ወንድም ወይም እህት-በተጠየቀው ት/ቤት ታላቅ ወንድም/እህት በ______ክፍል ይማራል/ትማራለች። የወንድም/እህት ስም ______________

☐ ቀደም ሲል በ COSA የፀደቀ መጋቢ ጥንድ/የተቀናጁ ኤለመንተሪ ት/ቤቶች፣ ወይም ከመካከለኛ ደረጃ ት/ቤት- ወደ ሁለተኛ ደረጃ ት/ቤት የድንበር/ወሰን ክልል ካልተቀየረ በስተቀር፣ የመቀጠል ውጥን/ፍላጎት። (ቀደም ሲል የፀደቀ የ COSA ቅጽ ከቀረበ ወዲያውኑ ሊጸድቅ ይችላል)

☐ በፑልስቪል ኤለመንተሪ ት/ቤት-Poolesville Elementary School የተመደበ/ች ተማሪ በሞኖካሲ ኤለመንተሪ ት/ቤት-Monocacy Elementary School ለመማር የሚፈልግ/የምትፈልግ ከሆነና የ COSA ቅጽ ካቀረበ/ች ወዲያውኑ ተቀባይነት ማግኘት ይቻላል።

የጥያቄ ቅጾች/ፎርሞች ከፌብሯሪ 1, 2018 በፊት አይቀርቡም እና ወይም ለ 2018–2019 የትምህርት ዓመት ከኤፕሪል 1, 2018 በኋላ አይቀርቡም። ያልታሰቡ/ልዩ ሁኔታዎች ካላጋጠሙ በስተቀር፣ ዘግይተው የደረሱ ማመልከቻዎች ተቀባይነት አይኖራቸውም።

በሌላ ሁኔታ ካልተገለጸ በስተቀር፤ ይህ ጥያቄ ከፀደቀ የሚከተሉትን እገነዘባለሁ፡- 1/ መጓጓዣ በሞንጎመሪ ካውንቲ የህዝብ ት/ቤቶች/Montgomery County Public Schools እንደማይሰጥ፤ 2/ ተማሪው/ዋ በሁለተኛ ደረጃ ትምህርት ቤቶች በተማሪዎች መካከል በሚደረጉ የአትሌቲክስ ውድድሮች ለአንድ አመት ለመሳተፍ ብቁ እንደማይሆን/እንደማትሆን፤ እና 3/ በበቂ ምክንያት COSA ሊሰረዝ እንደሚችል።

______________________________ ____/____/____
ፊርማ፣ ወላጅ/አሳዳጊ ቀን

**PART II: SCHOOL REVIEW. To be completed by the principal of student's home school.**

Residency Verification has been completed Date ____/____/____ MCPS Student ID # ______________

I have discussed this request with the parent/guardian Yes ☐ No ☐ School # ________

______________________________ ____/____/____
*Signature, Principal (Signature does not constitute agreement/disagreement with the request but does verify that residency has been validated.)* *Date*

**FORWARD TO:** Director, Division of Pupil Personnel and Attendance Services (DPPAS), 850 Hungerford Drive, Room 211, Rockville, MD 20850

**PART III: DPPAS ACTION. To be completed by DPPAS.**

Forwarded to: Consortium Office ☐ Special Education ☐ *Date* ____/____/____

**DPPAS Decision:**

☐ Approved ☐ Approved, to the end of school year ____ ☐ Denied–No unique hardship documented

Comments: ______________________________

______________________________ ____/____/____
*Signature, Director or Coordinator, DPPAS* *Date*

**ይግባኞች፡-** በ DPPAS ውድቅ ከተደረገ፣ ውሳኔው በተሰጠ 15 የካላንደር ቀናት ውስጥ ለ- Office of the Chief Operating Officer, Montgomery County Public Schools, 850 Hungerford Drive, Room 43, Rockville, Maryland 20850 በጽሑፍ ይግባኝ መቅረብ አለበት (እባክዎ ምክንያቱንና ሌላም ተጨማሪ ኢንፎርሜሽን/መረጃ ካለ ይግለጹ)። .

የዳወንካውንቲ ኮንሰርሽየም/DOWNCOUNTY CONSORTIUM

ሞንጎመሪ ብሌር (MONTGOMERY BLAIR)፣ አልበርት አንስታይን (ALBERT EINSTEIN)፣ ጆን ኤፍ ኬኔዲ (JOHN F. KENNEDY)፣ ኖርዝ ውድ (NORTHWOOD) ዊህተን (WHEATON)

የመካከለኛ ደርጃ ት/ቤት ማግኔት ኮንሰርሽየም

ARGYLE, A. MARIO LOIEDERMAN, PARKLAND

ኖርዝኢስት ኮንሰርሽየም (NORTHEAST CONSORTIUM)

ጄምስ ሁበርት ብሌክ (JAMES HUBERT BLAKE)፣ ፔይንት ብራንች (PAINT BRANCH)፣ ስፐሪንግ ብሩክ (SPRINGBROOK)

አድራሻ፦
11721 Kemp Mill Road
Silver Spring, Maryland 20902
301-592-2040

አድራሻ፦
DEPARTMENT OF SPECIAL EDUCATION SERVICES
850 Hungerford Drive
Room 230
Rockville, Maryland 20850
301-279-3837

# የሞንጎመሪ ካውንቲ የሕዝብ ት/ቤቶች (MCPS) የፀረ-መድሎ መግለጫ
# MCPS Nondiscrimination Statement

የሞንጎሞሪ ካውንቲ የሕዝብ ት/ቤቶች (MCPS) ዘርን፣ ጎሳ፣ ቀለም፣ የዘር ሃረግ፣ የብሔር ማንነት፣ ኃይማኖት፣ የስደተኝነት ሁኔታ፣ ጾታ፣ ስነ-ጾታ፣ የጾታ ማንነት (gender identity)፣ የጾታ አገላለጽ (gender expression)፣ የጾታዊ ግንኙነት ዝንባሌ/ምርጫ (sexual orientation)፣ የቤተሰብ/የወላጆች የኑሮ ደረጃ/አቋም/ሁኔታ፣ የጋብቻ ሁኔታ፣ እድሜ፣ ድህነት፣ እና የማህበራዊ ኤኮኖሚያዊ አቋም፣ ቋንቋ፣ የአካል ወይም የአእምሮ ጉዳተኝነት፣ በህገመንግስት ጥበቃ የተደረገላቸው ሁኔታዎችን ባህሪያትን ወይም ተዛማጅነት ያላቸውን (affiliations) መሠረት ያደረገ ሕገ-ወጥ አድሎ/መድሎ ይከለክላል። መድሎ ወይም አድሎአዊነት፤ በሕብረተሰባችን ለረዥም ጊዜ እኩልነትን፣ ፍትሕ፣ አብሮነት፣ሁሉን አቀፍነትን፣ ለመፍጠርና ለማሳደግ/ለመንከባከብ፣ ሲደረግ የቆየ ትጋትን ይሸረሽራል/ያበላሻል። አድልዎ የሚከተሉትን የተወሰኑ ምሳሌዎችን ያካትታል፦ጥላቻ፣ ሁከት፣ ደንታቢስነት፣ ወከባ፣ ማስፈራራት፣ ማሸማቀቅ፣ ንቀት፣ ወይም ማጥቃት። የበለጠ መረጃ ለማግኘት፣ እባክዎ የሞንጎመሪ ካውንቲ የትምህርት ቦርድ ደምብ/Policy ACA ስለ ጸረ-መድሎ፣ ፍትህ፣ የዳበረ ባህል ይመርምሩ። ይህ መመርያ እያንዳንዱ ተማሪ አስፈላጊ/ተፈላጊ መሆኑ(ኗ)ን፣ በተለይም የትምህርት ውጤቶች የሚረጋገጡት በምንም ዓይነት ግለሰብ ባለበት(ባለባት) ምክንያት ወይም ይሆናል ተብሎ የሚገመት ግላዊ ጠባዮች የሚተነበዩ አለመሆናቸውን የቦርዱን እምነት ያረጋግጣል። ፖሊሲው በቅድሚያ መወሰድ ስላለባቸው የፍትህ እርምጃዎች የተዛባ አመለካከትን፣ ማረጋገጫ የሌላቸው የማዳላት/ልዩነት አፈጻጸሞችን የሚያስከትሉትን አሉታዊነት፣ የትምህርት እና የሥራ መቀጠር እኩልነትን የሚያሰናክሉ መዋቅራዊ እና ድርጅታዊ አሠራር ደንቃራዎችን በተለይ ያስገነዝባል።

| በMCPS ሰራተኛ* ላይ ስለደረሰ መድሎዎ ጥያቄዎች ወይም ቅሬታዎች ለማቅረብ | በMCPS ተማሪዎች ላይ የአድልዎ ጥያቄዎች ወይም ቅሬታዎች ካላችሁ* |
|---|---|
| የሰራተኛ ተሳትፎ እና የሥራ ግንኙነት ጽ/ቤት<br>የአፈጻጸም እና የክትትል/የምርመራ መምሪያ Department of Compliance and Investigations<br>850 Hungerford Drive, Room 55<br>Rockville, MD 20850<br>240-740-2888<br>OCOO-EmployeeEngagement@mcpsmd.org | ት/ቤት አስተዳደር ጽ/ቤት Office of School Administration<br>የት/ቤት አስተዳደር ጽ/ቤት የአፈጻጸም ክፍል Office of School Administration Compliance Unit<br>850 Hungerford Drive, Room 162<br>Rockville, MD 20850<br>301-279-3444<br>OSSI-SchoolAdministration@mcpsmd.org |

* ክትትል፣ ቅሬታ/ስሞታ፣ ወይም ስንክልና ላለባቸው ተማሪዎች አመቺ ስፍራ ለመጠየቅ፤ ወደ ልዩ ትምህርት ተቆጣጣሪ ጽ/ቤት፣ የቅሬታ ሰሚና መፍትሔ ሰጪ ን/ክፍል በ ስልክ ቁጥር 301-517-5864 ሊቀርብ/ሊመራ ይችላል። ለሰራተኞች መገልገያዎች ወይም ማሻሻያዎች በሚመለከት የሚቀርቡ ጥያቄዎች ወደ Office of Employee Engagement and Labor Relations, Department of Compliance and Investigations/ የሰራተኛ ተሳትፎ እና የስራ ግንኙነት የአፈጻጸም እና የክትትል (የምርመራዎች) መምርያ፣ ስልክ፦ 240-740-2888 ሊመሩ ይችላሉ። በተጨማሪ፣ አድሎአዊነት ቅሬታዎች ለሌሎች ኤጀንሲዎችም ፋይል ሊደረጉ ይቻላል። እነርሱም፦ the U.S. Equal Employment Opportunity Commission, Baltimore Field Office, City Crescent Bldg, 10 S. Howard Street, Third Floor, Baltimore, MD 21201, 1-800-669-4000, 1-800-669-6820 (TTY); ወይም U.S. Department of Education, Office for Civil Rights, Lyndon Baines Johnson Dept of Education Bldg., 400 Maryland Avenue, SW, Washington, DC 20202-1100, 1-800-421-3481, 1-800-877-8339 (TDD), OCR@ed.gov, ወይም www2.ed.gov/about/offices/list/ocr/complaintintro.html.

ይህ ሠነድ ካስፈለገ በሚያቀርቡት ጥያቄ መሠረት ከእንግሊዝኛ በሌሎች ቋንቋዎችና በሌላ አማራጭ ቅርፀት ሊገኝ ይችላል። በአካል ጉዳተኝነት ስለሚኖሩ አሜሪካውያን ደንብ የሞንጎመሪ ካውንቲ የሕዝብ ት/ቤቶች የህዝብ ኢንፎርሜሽን እና የድረ-ገጽ አገልግሎት ክፍልን በስልክ ቁጥር፦ 240-740-2837, 1-800-735-2258 (ሜሪላንድ ማዞሪያ), ወይም PIO@mcpsmd.org. የምልክት ቋንቋ ትርጉም የሚፈልጉ ግለሰቦች ወይም የንግግር ትርጉም/ምልክት አገልግሎት ለማግኘት የሞንጎመሪ ካውንቲ የህዝብ ት/ቤቶች የትርጉም አገልግሎት ጽ/ቤት በስልክ ቁጥር፦ 240-740-1800, 301-637-2958 (VP) ወይም Interpreting_Services@mcpsmd.org መገናኘት ይችላሉ። የሞንጎመሪ ካውንቲ የሕዝብ ት/ቤቶች (MCPS)፤ ወጣት ስካውቶችን (ወንድ/ሴት) እና ሌሎችም የሚመለከታቸውን ወጣት ቡድኖችን በእኩል ያስተናግዳቸዋል።

በDepartment of Materials Management for the Office of the Chief Operating Officer የታተመ

ትርጉም፦ Language Assistance Services Unit • Office of Communications

0494.18ct • Editorial, Graphics & Publishing Services • 12/17 • NP